ምዕራፍ አራት
በርግጥ ተኣምር እውን ሊሆን ይችላልን?

መጽሐፍ ቅዱስ በተኣምራት የተሞላ መጽሐፍ ነው። ሙሴ በቀይ ባሕር ላይ እጁን ሲዘረጋ ባሕሩ ተከፈለ፤ እስራኤላውያንም በደረቅ ምድር ተሻገሩ። ሙሉ ቀን ለሚሆን ጊዜ ፀሓይ በሰማይ ዐናት ላይ ቆመች። ኤልሳዕ የብረት መጥረቢያ በውሃ ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገ። ኢየሱስ ክርስቶስ የዐይነ ስውራንን ዐይን አበራ፤ ሽባውን ተረተረ፤ ባልንጀራውን አልዓዛርን ከሙታን አስነሣ፤ በውሃ ላይ ሄደ፤ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ቀየረ፤ ሁለት ዓሣንና አምስት እንጀራን ለአምስት ሺህ ሰው መገበ ወዘተርፈ። ይህ ምዕራፍ፣ አንዳንድ የፍልስፍና ምሁራን ተኣምር እውን መሆን የሚችል ነገር አይደለም ለማለት ለሚያቀርቧቸው ሙግቶች መልስ ይሰጣል[1]።

1. ተኣምራት በብሉያትና በሐዲሳት

ቅዱሳት መጻሕፍት ተኣምርን ለመግለጽ "ምልክት"፣ "ድንቅ" እንዲሁም "ኀይል" የሚሉትን ሦስት ቃላት በተለዋዋጭነት ይጠቀማሉ። ብሉያት አንዳንድ ጊዜ "ምልክት" (ዕብራይስጥ "ኦት") የሚለውን ቃል ተፈጥሮአዊ ለሆኑ ክሥተቶችም የሚጠቀሙ ቢሆንም [ለምሳሌ:— ከዋክብትን (ዘፍጥረት 1÷14)፣ ሰንበትን (ዘፀአት 31÷13)] አብዛኛውን ጊዜ ግን፣ ልዩ የሆነ ምልክት ወይም ትርጒም በሚያስተላልፍ መልኩ ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል። እግዚአብሔር ሙሴን፣ "'እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እኔ የላክሁህ ለመሆኑ ምልክቱ ይህ ነው፤ ሕዝቡን ከግብፅ ካወጣሃቸው በኋላ በዚህ ተራራ ላይ እግዚአብሔርን ታመልካላችሁ' አለው" (ዘፀአት 3÷12)። ሙሴም "'ባያምኑኝስ፤ ቃሌን ባይቀበሉስ'" ብሎ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ እግዚአብሔር "ምልክትን" ሰጠው፤ ይኸውም በትሩ ወደ እባብ እንደምትቀየር (ዘፀአት 4÷3) እንዲሁም እጁን ወደ ብብቱ ሲያስገባ እንደ በረዶ ለምጽ መሆኗ መልሶ ወደ ብብቱ ሲያስገባ እንደ ሌላው ሰውነት የመሆን "ምልክት" ሰጠው (ዘፀአት 4÷1-7)። እነዚህ ተኣምራዊ ምልክቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሙሴ የተሰጡበት ዐቢይ ምክንያት እግዚአብሔር የገለጸው በዚህ መልኩ ነው፣ "የአባቶቻቸው አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር የተገለጠልህ መሆኑን እንዲያምኑ ነው' አለው" (ዘፀአት 4÷5)። "እግዚአብሔርም፣ 'እንግዲህ ባያምኑህ ወይም የመጀመሪያውን ታምራዊ ምልክት ባይቀበሉ እንኳ ሁለተኛውን ያምናሉ። እነዚን ሁለት ምልክቶች ባያምኑ ወይም ቃልህን ባይቀበሉ ግን፣ ከዐባይ ወንዝ ጥቂት ውሃ ቀድተህ በደረቅ ምድር ላይ አፍስሰው። ከወንዙም ቀድተህ ያፈሰስኸው ውሃ በምድር ላይ ደም ይሆናል'" (ዘፀአት 4÷8)። "ታምራቱንም በሕዝቡ ፊት አደረገ። ሕዝቡም አመኑ፣ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ የሚገደው መሆኑንና መከራቸውን ማየቱን በሰሙ ጊዜ ተንበረከኩ፤ በስግደትም አመለኩት" (ዘፀአት 4÷30-31)።

በእነዚህ ምንባባት በስፋት የተገለጸው እውነት ተኣምራት ሁለት ዐቢይ ትእምርት ሊወክል እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ይኸውም፣ ***አንደኛ:—*** "እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ በዚህ ታውቃለህ" (ዘፀአት 7÷17፤ 9÷29-30፤ 10÷1-2)፤ ***ሁለተኛ:—*** ይህም ሕዝብ የእኔ ሕዝብ እንደ ሆነ በዚህ ምልክት ትረዳለህ (ዘፀአት 3÷10፤ 5÷1፤ 6÷7፤ 11÷7)። ***ሦስተኛ:—*** እግዚአብሔር አምላክ ተኣምራቱን ባበዛው መጠን የፈርዖን ልብ የደነደነ ቢሆንም እንኳ (ዘፀአት 7÷3:5፤ 11÷9)፣ እግዚአብሔር ግን ባደረገው ሥራ ክብርን ተቀብሏል (ዘኍልቍ 14÷22)።

[1] የተኣምራትን ፍልስፍናዊ ገጽታ በስፋት መመልከት ከፈለጉ አባሪ አንድን ይመለከቷል።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ይህ ዐይነቱን “ምልክት” በሰዎች ሁሉ ፊት በማድረግ ሕዝቡን ከባርነት ዐርነት ሊያወጣ እንዳቀደ በርካታ ምንባባት በግልጽ ያስረዳሉ። በምድረ በዳ፣ “እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል? እነዚህን ሁሉ ታምራት በመካከሉ እያደረግሁ የማያምንብኝስ እስከ መቼ ነው?” (ዘኍልቍ 14÷11:22)። ሙሴም እስራኤላውያንን እንዲህ ሲል ሞግቶአቸዋል፣ “አምላካችሁ እግዚአብሔር በዐይናችሁ እያያችሁ ለእናንተ በግብፅ እንዳደረገው ሁሉ በፈተና፣ በታምራዊ ምልክቶችና በድንቆች፣ በጦርነት፣ በጸናች እጅና በተዘረጋች ክንድ ወይም በታላቅና በአስፈሪ ሥራዎች ከሌላ ሕዝብ መካከል አንድን ሕዝብ የራሱ ለማድረግ የቻለ አምላክ አለን?” (ዘፀአት 4÷8) ። “እግዚአብሔር በብርቱ እጅና በተዘረጋች ክንድ፣ በታላቅ ድንጋጤ፣ በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ከግብፅ አወጣን” (ዘዳግም 26÷8፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዘዳግም 29÷2-3፤ ኢያሱ 24÷17፤ ነህምያ 9÷10፤ መዝሙር 105÷27፤ ኤርምያስ 32÷20-21)።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አንድን ነቢይ ለአገልግሎት ሲጠራው ለአገልግሎት መጠራቱን የሚያረጋግጥበትን ምልክት እግዚአብሔር ይሰጠው ነበር። ሙሴ (ዘፀአት 4)፣ ጌዴዎን (መሳፍንት 6÷17:21)፣ ሳዖል ለንጉሥነት መሾሙ (1ሳሙኤል 10÷7:9፤ 9÷29-30፤ 10÷1-2)፣ ኢሳይያስ ትንቢቱ የእግዚአብሔር ለመሆኑ ምልክትን ሰጥቶ ነበር (ኢሳይያስ 7÷14፤ 38÷22)።

እግዚአብሔር ሐሰተኛ ሰዎችን ለመገሠጽ ተኣምራዊ “ምልክት” ሰጥቶአል። በቆሬ፣ በዳታንና አቤሮን (ዘኍልቍ 16)፣ የዔሊ ልጆች ተኣምራዊ በሆነ ሁኔታ እንደሚሞቱ (1ሳሙኤል 2÷34)፣ በግብፃውያን ላይ የወረደው መቅሠፍት (ዘፀአት 7÷3)፣ ኤልያስ በሐሰተኞቹ በበኣል ነቢያት ላይ (1ነገሥት 18)።

በብሉይ ኪዳን ምልክትና ተኣምራት የሚሉት ቃላት በአንድ ዐውድ ውስጥ በተለዋዋጭነት ተጠቅሰው እናገኛለን (ዘፀአት 7÷3፤ 4÷21፤ 11÷9-10፤ ዘዳግም 4÷34፤ 7÷19፤ 13÷1-2፤ 26÷8፤ 28÷46፤ 29÷3፤ 34÷11፤ ነህምያ 9÷10፤ መዝሙር 135÷9፤ 78÷43፤ 105÷27፤ ኤርምያስ 32÷20-21፤ ኢዩኤል 2÷30)።

በዕብራይስጥ “ኀይል” የሚለው ቃል ("ኮሃ")፣ አንዳንድ ጊዜ የሰብአውያንን ጉልበት ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም (ዘፍጥረት 31÷6፤ ዘዳግም 8÷17፤ ነህምያ 2÷1)፣ በአብዛኛው ግን አምላካዊ ኀይል የሆነውን ተኣምር ለማሳየት አገልግሎአል (ዘፀአት 15÷6-7፤ ዘኍልቍ 14÷17:13፤ 1ዜና 29÷12፤ መዝሙር 111÷6፤ ሚክያስ 3÷8፤ ኤርምያስ 10÷12፤ 32÷17፤ 51÷15)።

እንደ ብሉያት ሁሉ የሐዲስ ኪዳን ምንባባትም ተኣምርን ለማሳየት፣ “ምልክት” (ግሪክ “ሴሚዮን” “σημεîον”) የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። በሐዲስ ኪዳን ግሪክ “ምልክት” የሚለው ቃል ሰባ ሰባት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ አርባ ስምንት ጊዜ የተጠቀሰው በወንጌላት ላይ ነው። ቃሉ አንዳንድ ጊዜ የተለመዱ ሁኔታዎችን ለማሳየት ጥቅም ላይ ቢውልም እንኳ (ሮሜ 4÷11፤ ሉቃስ 2÷12)፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን ልእለ ተፈጥሮአዊ የሆነውን ተኣምር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል። እንዲያውም ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው የኢየሱስ ክርስቶስን ተኣምር ለማመልከት ነው። ይኸውም ሰዎችን መፈወሱ (ዮሐንስ 6÷2፤ 9÷16)፣ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩ (ዮሐንስ 2÷11)፣ ሙታንን ማስነሣቱ (ዮሐንስ 11÷47)። በተመሳሳይ መልኩ የክርስቶስ ሐዋርያት ያከናወኗቸው ተኣምራት ምልክት ተብለዋል (ሐዋርያት ሥራ 4÷16:30፤ 14÷3፤ 15÷12፤ 2÷43)።

በሐዲስ ኪዳን እጅግ ዋነኛ የተባለው የክርስቶስ ኢየሱስ ትንሣኤ ምልክት ተብሎአል፣ “ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ

ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ ዐንበሪ ኾድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቈየ እንዲሁ የሰው ልጅ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ኾድ ውስጥ ይቈያል" (ማቴዎስ 12÷39-40)። ኢየሱስ ምልክት እንዲያሳይ ሰዎች ጥያቄ ባቀረቡለት ጊዜ የሰጠው ምላሽ ትንሣኤው ትልቅ ምልክት እንደ ሆነ ነበር (ማቴዎስ 16÷1:4። የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ "ምልክት" ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ራሱ ትንቢት የተናገረለት ዐቢይ ክሥተት ነው (ማቴዎስ 12÷40፤ 16÷21፤ 20÷19)።

በሐዲስ ኪዳን ምንባባት "ድንቅ" የሚለው ቃል (ግሪክ "ቴራስ" "τέρας") ዐሥራ ስድስት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የዋለው ተኣምርን ለማመልከት ነው[2]። እንዲያውም በአብዛኛው ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው "ምልክት" ከሚለው ቃል ጋር ተደብሎ ሲሆን፣ የክርስቶስም ሆነ የሐዋርያቱ የሠሩትን ተኣምር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎአል (ዮሐንስ 4÷48፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷22፤ 2÷43፤ 4÷30፤ 5÷12፤ 6÷8፤ 14÷3፤ 15÷12፤ ሮሜ 15÷19፤ ዕብራውያን 2÷3-4፤ ማቴዎስ 24÷24፤ ማርቆስ 13÷22፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷9)። በሐዲስ ኪዳን "ኀይል" (ግሪክ "ዱናሚስ" "δύναμις") የሚለው ቃል ተኣምራትን ለማመልከት በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል። ቃሉ ዐልፎ ዐልፎ የሰብአውያንን ኀይል (2ቆሮንቶስ 1÷8) ወይም ችሎታ (ማቴዎስ 25÷15) እንዲሁም አንዳንዴ ሰይጣናዊ ኀይልን (ሉቃስ 10÷19፤ ሮሜ 8÷38) ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም፣ በአብዛኛው ግን እንደ ብሉይ ኪዳኑ ከአምላክ የሆነን ተኣምር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል። እንዲያውም በበርካታ ቦታዎች ላይ ከምልክትና ከድቅን ጋር ተያይዞ ተጠቅሶአል (ዕብራውያን 2÷4)። "ኀይል" (ግሪክ "ዱናሚስ" "δύναμις") የሚለው ቃል የኢየሱስን ያከናወነውን ተኣምር (ማቴዎስ 13÷58)፣ ሙታንን ለማስነሣት ያስቻለን ኀይል (ፊልጵስዩስ 3÷10)፣ ክርስቶስ ከድንግል መፀነሱን (ሉቃስ 1÷35)፣ ተኣምራት የማድረግን ስጦታ (1ቆሮንቶስ 12÷10)፣ በባዓለ ኀምሳ ቀን የወረደውን መንፈስ ቅዱስን (ሐዋርያት ሥራ 1÷8)፣ ኀጢአተኞችን የሚያድነውን የወንጌል ኀይል (ሮሜ 1÷16)።

፪. የተኣምራት ፋይዳ ምንድን ነው

እነዚህንና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጒዳዮች በስፋት ከመመልከታችን በፊት፣ እግዚአብሔር አምላክ ተኣምራት እውን እንዲሆኑ የሚያደርግባቸውን አንኳር አንኳር ምክንያቶች እንቃኝ።

በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ተኣምራት ፈርጀ ብዙ የሆነ ትርጒምም ሆነ ጠቀሜታ አላቸው። (1) ታኣምራት ተዘውትሮ ከሚከሠተውና በተፈጥሮ ሕግጋት ከሚተዳደረው ተፈጥሮአዊ አካሄድ ፍጹም የተለዩ ናቸው። ተኣምር ከተፈጥሮ ሕግጋት ውጪ የሆነ ድንቅ ክሥተት የመሆኑ ጒዳይ፣ የሰውን ልቡናና አእምሮ የመማረክ ጠባይ አለው። (2) ተኣምራት የእግዚአብሔር ሥራዎች ስለሆኑ፣ በሚከሠቱበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን አልሆት ያጣቅሳሉ፤ ምክንያቱም ሁል ጊዜ ተኣምር ከተፈጥሮ ሕግጋት ውጪ የሆነ ልዕለ ተፈጥሮአው ክሥተት በመሆኑ። (3) ተኣምራት የእግዚብሔርን ባሕርይ የመግለጽ ችሎታ ስላላቸው ፍጥረታት እግዚብሔርን እንዲያከብሩ ያደርጋሉ። እግዚአብሔር መልካም አምላክ በመሆኑ የሚሠራቸውም ማናቸውም ዐይነት ሥራዎች እጅግ መልካም ናቸውና። (4) ተኣምራት አስተምህሮአዊ ፋይዳ ስላላቸው ነገረ መለኮትን ለማዋቀር ጠቀሜታቸው ትልቅ ነው። ለምሳሌ:— ተኣምራት ሐሰተኛ ነቢያትን ከእውነተኛ ነቢያት የምንለይባቸው መስፈርት ናቸው (ዘዳግም 18÷22)። የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት መቀበላቸውን ይፋ ለማድረግም ተኣምራት ጠቀሜታ ላይ የዋሉበት ሁኔታ አለ (ዕብራውያን 2÷3-4)። (5) ተኣምራት እንደ ጥንቈላ ሰዎችን ለማስደነቅ ወይም ለማዝናናት የሚከሠቱ ክሥተቶች ሳይሆኑ (ሉቃስ 23÷8)፣

---

[2] ቃሉ አንድ ጊዜ ብቻ ሰይጣናዊ የሆነውን ምልክት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሎአል (2ተሰሎንቄ 29)።

ሰዎች በአልሆተ እግዚአብሔር እንዲያምኑ፣ አምላክን እንዲያከብሩ እንዲሁም የእግዚአብሔርን እውነት እንዲቀበሉ መረጋገጫ ይሰጣሉ[3]።

3. "ተኣምር" ማለት ምን ማለት ነው?

አሁን ደግሞ "ታኣምር" ማለት ምን ማለት ነው፣ የሚለውን ጉዳይ እንመልከት። በርካታ ውይይቶች ፍሬ አልባ ከሚሆኑባቸው ዐቢይ ምክንያቶች መኻል አንዱ፣ ለውይይቶቹ ቊልፍ የሆኑ ቃላት ትክክለኛ ትርጒም ስለማይሰጣቸው፣ እነዚህ ቃላት ሐሳቡን የሚሸከሙ ሠረገሎች ከመሆናቸው ይልቅ ውይይቱን በማደፍረስ የጠራ ምልከታ እንዳይኖር እክል መፍጠራቸው ነው። የእኛም ጥረት ንፋስ የመጐሰም ዐይነት እንዳይሆን፣ ፍልስፍና ገጽታውን ለመመርመር ስንነሣ ቃሉን በትክክል በመተርጐም ወደ ውይይታችን እንዝለቅ።

አፍሪካዊው የነገረ መለኮት ሊቅ ቅዱስ አውጉስጢኖስ፣ "ተኣምር እንደ ምልክት ሲሆን ይህም ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር የሚቃረን ሳይሆን፣ እኛ ስለ ተፈጥሮ ሕግጋት ካለን ዕውቀት የሚጋጭ ክሥተት ነው"[4]። ከአውጉስጢኖስ በኋላ በርካታ ምሁራን ተኣምር ተፈጥሮ ሊከሥተው የማይችል፣ መለኮታዊ አካል ግን እውን ሊያደርገው የሚችል ክሥተት ነው ሲሉ ተርጒመዋል። በአጠቃላይ ተኣምር ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር የሚጣረስ ሳይሆን፣ አምላክ ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር በማይጣረስበት ሁኔታ በተፈጥሮ ውስጥ ጣልቃ የመግባቱ ክሥተት ነው። "የተፈጥሮ ሕግጋት የምንለው በተፈጥሮ ሕግጋት መንሥኤነት ተደጋግሞ የሚከሠተውን ክሥተት ሲሆን፣ ተኣምር ደግሞ በአምላክ ክንዋኔ እውን የሚሆን ተደጋግሞ የማይከሠት ክሥተት ነው"[5]።

4. "የተፈጥሮ ሕግ" ማለት ምን ማለት ነው?

ተኣምር ምንድን ነው የሚለውን ግላጼ የበለጠ ለማጒልበት፣ "የተፈጥሮ ሕግጋት" ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጒዳይ በመጠኑም ቢሆን መመልከት አግባብነት ይኖረዋል። "የተፈጥሮ ሕግጋት ማለት በተደጋጋሚነት፣ ሥርዐቱን በጠበቀ እንዲሁም አጠቃላይ በሆነ መንገድ በዓለማችን የሚተገበር ክሥተት ነው"[6]። ስለ ተፈጥሮ ሕግጋት ያስቀመጥነው ግላጼ፣ ተኣምር ምን እንደ ሆነም ፍንጭ የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ተኣምርንም የሚገልጽ ነው። ይኸውም ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ፣ "ተኣምር ማለት በተደጋጋሚነት፣ ሥርዐቱን በጠበቀ እንዲሁም አጠ ቃላይ በሆነ መንገድ የማይከሠት፣ አምላክ በዓለም ላይ እውን እንዲሆን የሚያደርገው ክሥተት ነው"[7]።

ፕሮፌሰር ኖርመን ጋይዝለር፣ ስመ ጥሩን የፊስክስ ሊቅ ሰር ጆርጅ ስቶክስ ያገኙትንና በስማቸው የሚጠራውን ሳይንሳዊ ሕግ በመጥቀስ፣ ስለ ተኣምር የሰጡትን ትንታኔ በዚህ መልክ አቅርበውታል፣ "ተኣምር ብለን የምንጠራው ክሥተት የተፈጥሮን ሕግጋት ቋሚ ተግባራቸውን የሚከውኑበትን ሕግ በማደናቀፍ የሚከሠት ክሥተት ሳይሆን፣ ከዕለት ተዕለት ክሥተታቸው

---

[3] Norman L. Geisler, *Miracles and the Modern Mind: A Defense of Biblical Miracles* (Grand Rapids: Baker, 1992), 98-99.

[4] Norman L. Geisler, *Miracles and the Modern Mind: A Defense of Biblical Miracles* (Grand Rapids: Baker, 1992), 14. ከAugustine, *City of God* 21.8 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[5] ዝኒ ከማሁ።

[6] ዝኒ ከማሁ።

[7] ዝኒ ከማሁ።

ተጨማሪ በሆነ መልኩ እውን የሚሆን ነው"[8]:: እስካሁን ከተነጋገርንበት እውነት የምንግረው ቀሩም ነገር፣ ተአምር የተፈጥሮ ሕግ መንሥኤና ተገብሮን ማዕከል ባደረገ መልኩ የሚከሠተውን ክሥተት የሚቃወም ወይም የሚጻረር ክሥተት ሳይሆን፣ በመለኮት ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ የሚሆን ተጨማሪ ክሥተት ነው::

5. የታአምራት እውን መሆን ከእግዚአብሔር አልሆት ጋር ይቃረናልን?

"ተአምር እውን ሊሆን የማይችል ክሥተት ነው" የሚሉ ሰዎች የሙግታቸው ፍሰት የሚከተለውን ይመስላል:—

(1) የተፈጥሮ ሕግጋት ሁሉ አጋኜ/ቀማሪ እግዚአብሔር ከሆነ፣
(2) እነዚህም የተፈጥሮ ሕግጋት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የማይቀየሩ ሕጎች ከሆኑ፣
(3) እግዚአብሔር የራሱን ሕግ የማይቃረን ከራሱም ጋር የማይጣረስ አምላክ ከሆነ፣
(4) ተአምራት እውን መሆን በፍጹም አይችልም[9]::

የዚህ ሙግት መሠረታዊ ችግር በሙግት ነጥብ ሁለትና በሙግት ነጥብ ሦስት ላይ ያለ ነው:: የሙግት ነጥብ ሁለትን በተመለከተ ልናነሣው የሚገባን መሠረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:— የተፈጥሮ ሕግጋት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የማይቀየሩ ለመሆናቸው አንዳችም ማስረጃ አለመቅረቡ አንደኛው ነጥብ ሲሆን፣ "ተአምራት የተፈጥሮ ሕግጋትን ይቃረናሉ" የሚለውን አምለካከት ታሳቢ ያደረገ ሙግት ነው:: ተአምራት የተፈጥሮ ሕግጋትን ለመቃረናቸው ምን ማስረጃ አለ? አንድ ሰው፣ "ተአምር አምላክ ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር በማይጣረስበት ሁኔታ በተፈጥሮ ውስጥ ጣልቃ የመግባቱ ክሥተት ነው" ብሎ ሚተረጕመው ስሕተት የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? ቍጥር ሦስትን በተመለከተ የሚታየው መሠረታዊ ችግር፣ አምላክ ተአምራትን ማድረጉ ከራሱ ጋር እንደሚቃረን ተደርጎ የመቅረቡ ጕዳይ ነው:: በርግጥ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የሚጻረር ነገር ያለማድረጉ እሙን ቢሆንም፣ ተአምራት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የሚጻረርበት ክሥተት ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ምንድን ነው? (ይቃረናል ከተባለ ለመቃረኑ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል):: አንድ ሰው በአንድ ወቅት በአንድ ስፍራ ያስቀመጠውን ዕቃ መልሶ ቢያነሣው ከራስህ ጋር ተጻረሃል የሚባልበት ምክንያት ምንድን ነው? የተፈጥሮ ሕግጋት ሁሉ አጋኜ/ቀማሪ እግዚአብሔር መሆኑ ከታመነ፣ ይህንን ሕግ በተወሰነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ላይ ተግባራዊ እንዳይሆን ማድረጉ ከራሱ ጋር እንደ መጻረር ተደርጎ የተወሰደበት ምክንያት ምንድን ነው? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በስፋት የምንሞግትበት የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የመነሣት ክሥተት ተአምራት እውን መሆን የሚችሉ ክሥተቶች መሆናቸውን የሚያመለክት ናሙና ነው::

አንዳንድ ሰዎች ሳይንስ ያልነገረኝን ነገር ስለማላምን ተአምራት እውን መሆን ይችላሉ ብዬ አላምንም ይላሉ:: ይህ ስሕተት የሚሆንበት ምክንያት፣ ሳይንስ ተደጋግሞ የሚከሠቱ ተፈጥሮአዊ ክሥተቶችን የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ስለሆነ፣ ተአምራት ደግሞ ተዘውትሮ የሚከሠት ተፈጥሮአዊ ክሥተት ስላልሆነ፣ ተአምር ሳይንስ ከሚያጠናው ወይም ሊደርስበትም ከሚችለው ክልል ውጪ ያለ የትምህርት ዘርፍ ነው::

---

[8] Norman L. Geisler, *Miracles and the Modern Mind: A Defense of Biblical Miracles* (Grand Rapids: Baker, 1992), 14. ከInternational Standard Bible Encyclopedia (Grand Rapids: Eerdmans, 1939), 2063. ጠቅሶ ከጻፈው የተወሰደ::

[9] ይህ በ1632 እስከ 1677 ዓ.ም የኖረው የቤኔዲክት ደ ስፒኖዛ የአምላክኛነት (deism) ፍልስፍናን ሙግት የተከተለ ሙግት ነው:: እንደ አምላከኛነት፣ "ሰዓት አንድ ጊዜ ከተሞላ በኋላ በራሱ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ ዓለምም አንዴ ከተፈጠረ በኋላ በራሱ ሕግጋት ይንቀሳቀሳል፤ እግዚአብሔርም በዚህ ውስጥ ጣልቃ አይገባም" የሚል ንጽርኦተ ዓለም ነው::

ፕሮፌሰር ኖርማን ጋይዝለር ይህን የሙግት ነጥብ በዚህ መልኩ አቅርበውታል[10]:—

(1) ሳይንሳዊ ዕውቀት ዘወትር መሠረት የሚያደርገው ተደጋግሞ በሚከሠቱ ክሥተቶች ላይ ነው፣
(2) ተኣምራት ተደጋግሞ የሚከሠቱ ክሥተቶች አይደሉም፣
(3) ስለዚህ ተኣምራት የሳይንስ የጥናት ዘርፍ የሚሸፍነው ክፍል አይደለም።

ሳይንስ መሠረት ያደረገበት ይህ አካሄድ ደግሞ የሚከተለውን መሠረተ ነጥብ ታሳቢ ያደርጋል:— በተፈጥሮ ሕግጋት ውስጥ ነገሮች ተደጋግመው መከሠታቸው የተፈጥሮ እእምሮአዊ የሆነ አካል በሥርዐት እንዳዋቀረው የሚያመለክት ነው።

አንዳንድ ሰዎች፣ “አዳዲስ ግኝቶችን በማግኘት የዕውቀት ባለቤቶች መሆን የምንችለው ሳይንሳዊ መሆኑ ጥናቶች ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶአል የሚለው ተኣምር በሳይንሳዊ ፍተሻ ውስጥ ተጣርቶ ያላለፈ ነው” የሚል አስተያየት አላቸው። ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ በርካታ ስሕተቶች አሉበት። ይኸውም:— (1) ሳይንሳዊ ዕውቀት የሚመሠረተው ተደጋግሞ በሚከሠቱ ክሥተቶች ላይ ብቻ ስለሆነ፣ ታሪክን መሠረት ያደረጉ ክሥተቶችን በሳይንስ መፈተሽ አይቻልም። ምክንያቱም ታሪካዊ ክሥተቶች ተደጋጋሚ ባለመሆናቸው እንዲህ ወይም እንዲያ ይሆናሉ ብሎ መተንበይ በጭራሽ አይቻልም። ይህ ደግሞ ሳይንስ የራሱ የሆነ ዳር ድንበር እንዳለው የሚያሳየን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ታሪካዊ ክሥተት ስለሆነ በሳይንስ መስፈርት ልንመረምረው አንችልም። (2) ልክ እንደ ታሪካዊ ክሥተቶች ሁሉ ተኣምራት ተደጋግመው የሚከሠቱ ክሥተቶች ባለመሆናቸው፣ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ያሉትን ተኣምራት በሳይንስ መመርመር አንችልም። ይህም ሳይንስ የራሱ የሆነ ክልል እንዳለው የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ሁሉ ነገር በሳይንስ በኩል ካልመጣ አልቀበልም ማለት የሳይንስን ዐቅም በቅጡ ያለመረዳት ነው። (3) በርግጥ የዓለማት ፈጣሪ እግዚአብሔር ካለ ተኣምራትን ማድረግ የሚከለክለው ምክንያት ምንድን ነው? እግዚአብሔር አምላክ አልሆትም ሆነ፣ ተኣምራትን እውን ማድረግ የሚችል አምላክ መሆኑን በግልጽ መረዳት የምንችልበት ጥሩ ናሙና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው። ታሪክ ነባራዊ ገጽታ ያለው የጥናት ዘርፍ እስከ ሆነ ድረስ፣ አንድን ታሪክ ትክክለኛ ታሪክ ለመሆኑ የታሪክ ምሁራን የሚጠቀሙበትን መስፈርት በመጠቀም የክርስቶስ ትንሣኤን በመመርመር እውነታውን ማግኘት ይቻላል።

ሌሎች ደግሞ፣ “የሞቱ ሕዋሳት ዳግም ሕይወት እንደማያገኙ ሳይንስ በግልጽ ስለሚስተምር ከዚህ ጋር በተጻረረ መልኩ የሞተ ሰው ዳግም ሕይወት ይዘራል ማለት ስሕተት ነው” የሚል አስተያየት ያቀርባሉ። ይህም አስተያየት የራሱ የሆኑ እክሎች አሉበት:— (1) የሞቱ ሕዋሳት ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ሕይወት ዳግም እንደማያገኙ ሳይንስ መግለጹ እሙን ነው፤ እኛም ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ሙታን ሕያው ይሆናሉ አላልንም። ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ/በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት እንጂ። ለዚህም ነው የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ነው የሚሉን (ለምሳሌ:— የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:— የሐዋርያት ሥራ 2÷24:32፤ 3÷15:26፤ 4÷10፤ 10÷40፤ 13÷30:37፤ ሮሜ 10÷9፤ ገላትያ 1÷1፤ 1ተሰሎንቄ 1÷10፤ ዕብራውያን 13÷20፤ 1ጴጥሮስ 1÷21)። (2) ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱ ታሪካዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ይዘትም አለው። ይህ ማለት መነሣቱ ታሪካዊ ሐቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ አምላክ ነኝ ለሚለው ንግግሩ

[10] Norman L. Geisler, *Miracles and the Modern Mind: A Defense of Biblical Miracles* (Grand Rapids: Baker, 1992), 86.

ማስረገጫ (ዮሐንስ 2÷18-22፤ 10÷18) እንዲሁም ተኣምራትን ማድረግ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ነው[11]።

በአጠቃላይ የተለያዩ ንጽርኦተ ዓለሞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ፣ ተኣምራት እውን ሊሆን የማይችል ክሥተት ነው የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቧቸው የተለያዩ የሙግት ነጥቦች ድምዳሜያቸውን የሚያጸና አይደለም።

[11] ኢየሱስ ተኣምራትን ያደርግ እንደ ነበር በሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን ብቻ ሳይሆን፣ በወቅቱ በነበሩ በታሪክ ጸሓፊዎች ሁሉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። አይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልድ ኮርዮን፣ ኢየሱስ “አስደናቂ ተኣምር የሚያደርግ ሰው ነው” ሲል ጽፎአል (*Antiquities* 18:3; 3:38; 9:58; 2:223, 285, 295, 345, 347; 3:1, 30, 38; 528; 9:58, 60; 10:214, 235; Against Apion 2:114)። አሮኖቢዩስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ዐቃቤ እምነት በ330 ዓ.ም አካባቢ በጻፈው ጽሑፍ ኢየሱስ በእርሱ ዘመን አጋንንት አስወጪው በመባል ይታወቅ እንደ ነበር ጽፎአል።